# ‹‹ኢሠፓአኮ - ባዶ ፓኮ››

ፍቃዱ ሐብተወልድ - ከኮተቤ *senaygerma29@gmail.com*

ሰዎች በብዛት በሚታዩበት፣ ሞቅ ደመቅ በሚባልበት ቦታ ሁሉ አይጠፋም፡፡ አእምሮው ጤነኛ አይደለም ቢባልም የሰዎችን ትኩረት ግን አያጣም፡፡ ብዙዎች እያንሾካሾኩም ቢሆን አባባሉን እየተቀባበሉ የጨዋታቸው ማድመቂያ ያደርጉታል፡፡

ዜጐች ሐሳባቸውን በነፃነት መግለፅ በማይችሉበት በዚያን ወቅት ታዲያ እንዳፈቀደው የልቡን የሚናገረው ይህ ግለሰብ ብዙ ጊዜ ታስሮ ብዙ ጊዜ ተገርፏል፡፡ ለምን አይታሰር፣ ለምን አይገረፍ፡፡ ‹‹ኢሠፓአኮ - ባዶ ፓኮ›› እያለ በየአደባባዩ እየጮኸ ይናገራል፡፡ ወዲያው ይታሰራል፣ ቆይቶም ይፈታል፡፡

አንዴ እንዲህ ሆነላችሁ ፡፡ ያኔ ፓርቲውንም ሆነ የባለሥልጣናቱን ስም በክፉ አሊያም በመጥፎ ማንሳት የቱን ያህል አስቸጋሪ እንደነበር ይታወሳል፡፡ ለዚህ ሰው ታዲያ ይኼ ምኑም አይደለም፣ ቁብ አይሰጠውም፡፡ አርቲፊሻል መሣሪያ ይዞና ፀጥታ ጠባቂዎችን በመላ አልፎ አደባባይ ወደተገኙት ባለሥልጣን ዘንድ ተጠጋ፡፡ የያኔውን የከፋ ክፍለ ሀገር የደርግ ከፍተኛ ባለስልጣን ስማቸውን ከነአባታቸው ተጣርቶ ‹‹እገሌ በላይ፣ እጅ ወደላይ፣›› ኣላቸው አሉ አርቲፊሻሉን መዝዞ፡፡ እንደፈረደበት ተይዞ ከርቸሌ ወረደ - ከድር ሰተቴ፡፡

ከድር ሰተቴ ሀሳቡን በግጥም መግለፅ የሚሳነው ሰው አይነት አልነበረም፡፡ ወደ እሥር ቤት ሲወረወር አርፎ አልተቀመጠም፡፡ ወዲያውኑ እንዲህ ነበር ያለው፡፡ ‹‹እኛ ያደረግነው ለቀልድ፣ እነሱ ያሉት የመግደል ሙከራ፣›› የሚገርም ሰው ነበር፡፡

ረዥም ወራትን እሥር ቤት አሳልፎ ኖሮ አጋጣሚ እኚሁ ባለሥልጣን ወህኒ ቤቱን ሲጎበኙ ከድር ሰተቴ ያያቸውና የባለሥልጣኑን ስም ከፍ አድርጎ ተጣርቶ ‹‹ እንቶኔ በላይ፣ ከሁሉም በላይ፣ ›› ብሎ ይላል ፡፡ ባለሥልጣኑም ሙገሳውን በውስጣቸው በመቀበል ‹‹እንዴ! ይኼ ሰው እስከዛሬ እዚህ ነው ያለው? በሉ ፍቱት ፡፡›› ብለው አዘዙ ፡፡ ከድር

ሰተቴም ከእስር ተፈታ፡፡ ጅማ ከተማ ውስጥ ከድር ሰተቴን የማያውቅ ሰው የለም፡፡ አሁን የት ይድረስ መጨረሻው ምን ይሁን እንጃ፡፡

ሰዎች በመናገራቸውና ሃሳባቸውን በመግለፃቸው ብቻ ይታሰሩ፣ ይገረፉና ይገደሉ የነበረበት ያ መጥፎ ዘመን ላይመለስ እስከወዲያኛው ተሰናብቶናል፡፡ ጤነኛው አይደለም አእምሮው ‹‹ንክ›› ነው የሚባለው ሳይቀር እንዲናገር የማይፈቀድበት ያ ስርዓት ላይመለስ እስከመጨረሻው አክትሟል፡፡

ዛሬ ዜጎች ባፈቀዷቸው ጉዳይ ተጠራርተው መመካከር፣ እንደየፍላጎታቸው መደራጀት፣ መቃወም፣ መደገፍ፣ ሃሳባቸውን ያለምንም ከልካይ በነፃነት የመግለጽ ዴሞክራሲያዊ መብቶቻቸው ተረጋግጦላቸል፡፡

ሃሳብን በሃሳብ የመሞገት፣ የማይመችና የማይጥም አስተሳሰብን የመንቀፍ ፣ የሚጐረብጥ አመለካከትን የመቃወም ነፃነቱ እንደዚያው እንደተጠበቀ ነው፡፡ ይህ የሚያግባባን ከሆነ አንድ ‹‹ጉምቱ›› የአገሬ ፖለቲከኛ የሰሞኑ ንግግር ግርምትን ቢፈጥርብኝ ነው ብእሬን ላነሳ የፈቀድኩት፡፡

የት ቦታ ምን አይነት ዲስኩር፣ ለእነማን ምን አይነት ንግግር ባደርግ ተሰሚነትና ተቀባይነት ሊኖረኝ ይችላል ብሎ ቀድሞ ማሰብ መቼም በፖለቲካ ትግል ውስጥ “የህይወቴን ግማሽ እድሜ በላይ አሳልፌያለሁ” እያለ የሚመፃደቅ የፖለቲካ አራማጅ ይኼ ይጠፋዋል ብሎ መገመት የዋህነት ነው፡፡

የአንድነት ፓርቲ ሰሞኑን በጠራው ጋዜጣዊ መግለጫ ላይ ከተሳተፉት የፓርቲው ‹‹ቱባ›› አመራሮች አንዱ አቶ ሥዬ አብርሃ ነበሩ፡፡ መልእክቱ የፓርቲው አቋም ይሁን የግለሰቡ በውል የታወቀ ነገር ስለሌለ አቶ ሥዬ የተናገሩት እያልኩ አስተያየቴን ልሰጥ እወዳለሁ፡፡

አቶ ሥዬ ከገዛ አንደበትዎ በድንገድ ሾልካ ይሁን ሆን ብለው አስበውበት የወጣችውን ሆኖም ድብቅ ውስጣዊ የጥላቻ አቋምዎን ያሳበቀችብዎትን ንግግርዎን አዳምጬዋለሁና ቃል በቃልም ቢሆን ልጠቅሰው እችላለሁ፡፡

‹‹ … ኢህአዴግ በተንቤን እኔን የሚያሸንፈኝ ተወዳዳሪ ሊያቀርብ አይችልም፤ በመቀሌ ገብሩን የሚያሸንፍ ተወዳዳሪ ሊያቀርብም አይችልም፡፡ ሥዬ በተንቤን ተሸንፏል ካሉ ለመስረቃቸው ትልቅ ማስረጃ ነው፡፡›› የሚል ነበር፡፡ የሚያሳፍር ነው፡፡

ለዚህ ወር የተለቀቀች አዲስ ነጠላ ዜማቸው መሆኗ ነው ልበል? ብዙ … ብዙ ያስብላል፡፡ የንግግራቸው ጭብጥ በደፈናው ሲፈተሽ በውስጡ የተለያዩ ሚስጥራዊ መልእክቶችን ለማስተላለፍ እንደሚሞክሩ በርካታ መላ ምቶችን መጠቃቀስ ይቻላል፡፡ አንድ ሁለት እንበል፡፡

በምርጫው ዋዜማ ላይ ሆኖ ለሌሎች የአመፅ ተግባራት የመጀመሪያዋን የጥሪ ደወላቸውን እንደማሰማት ሊቆጠርላቸው ይችላል፡፡ ይህም ሲባል የምርጫውን የዘመቻ ሒደት ለአመፅ ማነሳሻ፣ ማደራጃና መቀስቀሻ ሊጠቀሙበት ዘይደውም ሊሆን ይችላል ተብሎ ይታሰባል፡፡

በአገሪቱ የሚካሄደውን ብሔራዊ ምርጫ ነፃ፣ ፍትሐዊ፣ ሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ አይደለም የሚል የማጨለሚያና የማጥቆሪያ ዘመቻዎችን በማካሄድ ሂደቱ በህዝቡ ዘንድ ተአማኒነት እንዳይኖረው በጥንቃቄ ተሰልታ የተደረገች ዲስኩር የማትሆንበት ምክንያትስ ምንድነው? ማን ያውቃል፡፡

የዚህ ስትራቴጂ ግብ ደግሞ በጣም ግልፅ ነው - የቀለም አብዮት፡፡ ምርጫ በሚካሄድባቸው ብዙዎቹ አገሮች የቀለም አብዮት አራማጆች የትግል ስልታቸው እንደምንም ብለው የሂደቱን ተአማኒነት ለማሳጣት ታች ላይ ማለት፤ ሂደቱን በማንኳሰስ ዋጋ ለማሳጣት መጣር ተደጋግሞ የታየ ጉዳይ ነው ፡፡

እንዲያም ሆኖ በምርጫው ፉክክር ውስጥ ይገባሉ፡፡ የቤት ስራዎቻቸውን በቅጡ ሳይከውኑና መልካም አማራጮችን ይዘው ሳይቀርቡ ቀርተው የህዝቡን ይሁንታ አጥተው ተሸናፊ ሲሆኑ ሰበብ ይደረድራሉ፡፡ ይኸው የፈራነው ደረሰ፡፡ አስቀድመን ገልፀን ነበር፡፡ "ምርጫው ተጭበርብሯል፡፡ ውጤቱንም አንቀበልም፡፡" የሚሉ ሃሰተኛ የፕሮፖጋንዳ ዘመቻዎችን በመንዛት በዚያች ሃገር ሁከት፣ ነውጥና ብጥብጥ በማነሳሳት ሌላኛውን ወደስልጣን የመውጫ መንገድን ይፈትሻሉ - የቀለም አብዮተኞች ፡፡ የአቶ ሥዬ ንግግር ጭብጥም ከዚህ አንፃር ሊገጣጠም እንደሚችል መጠርጠር አያስከፋም፡፡ ማን ያውቃል፡፡

ነገርን ነገር ያነሳዋል አይደል የሚባለው፡፡ የሆነ ጉዳይ ትዝ ብሎኝ ነው፡፡ ኸረ ለመሆኑ ለውስጠ ፓርቲ ዲስፐሊን ተገዥ ሆኖ፣ የሃሳብ ልዩነቶችን አቻችሎና በዴሞክራሲያዊ የችግሮች አፈታት ሥልት መላ ዘይዶ ከመንዝ ፈንታ በጠራራ ፀሃይ አዲስ አበባ ውስጥ በሚገኝ የአንድ ተቃዋሚ ፓርቲ ፅህፈት ቤት ውስጥ በፍልጥና ቆመጥ የተናረቱ፤ አሁን በዚያን ሰሞን ደግሞ በምስራቅ ወለጋ በአንድ የምርጫ ጣቢያ ‹‹እኔ ነኝ እጩ ፣ የለም አንተ አይደለህም›› በሚል መነሻ በቡጢ የተጐሻሸሙ እድል ቀንቷቸው አሸናፊ ሆነው ወደስልጣን ቢመጡ ለእኛ ምን አስቀርተውልን ይሆን? ፍልጡንም ቡጢውንም እነሱው ጨርሰውታልና! እባካችሁን የቤት ስራዎቻችሁን በቅጡ ከውኑ፡፡

ከድር ሰተቴ ዛሬ በህይወት ይኑር ይሙት አላውቅም ብያለሁ፡፡ ድምፁ ግን አሁንም ድረስ ውስጤ ዘልቆ ይሰማኛል - “ኢሡፓአኮ - ባዶ ፓኮ”፡፡ ዜጐች የመሰላቸውንና ያመኑበትን ሃሳብ በመግለፃቸው ክፉ እንዲገጥማቸው አልመኝም፡፡ አቶ ሥዬም ያደረጉትን ንግግር ደጋግሜ ሰምቻለሁ፡፡ ለምን ተናገሩ ተቃውሞ የለኝም - ህገ መንግስታዊ መብታቸው ነው፡፡ እሳቸውም ቢሆኑ በንግግሬ ላይ ለምን አስተያየት ተሰጠበት ብለው ቅር ሊሰኙ አይገባም - ሃሳቤን የመግለፅ ሙሉ መብት እንዳለኝ ይረዳሉ ብዬ እገምታለሁ፡፡

ሙግቴን ልቀጥል፡፡ ‹‹በዚህ የምርጫ ክልል ድል አደርጋለሁ፤ ባለኝ ዝግጅትና የተሻለ አማራጭ ፕሮግራም አሸናፊም ሆኜ እወጣለሁ፡፡›› ብሎ ማለት የአባት፡፡ የከፋው ነገር ‹‹በውድድሩ እኔ ከተሸነፍኩ ኮሮጆ ተገልብጧል፤ ምርጫውም ተጭበርብሯል›› ብሎ መደምደም ደግሞ ትልቁ ስህተት፡፡

ለአንድ የምክር ቤት መቀመጫ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ እጩዎች በአንድ ጊዜ ተወዳድረው አሸናፊ ሆነው የወጡበት ሁኔታ እስከ ዛሬ አላጋጠመኝም፤ አልሰማሁምም፡፡ ያ ከሆነማ ዴሞክራሲያዊ ምርጫን ማካሄዱ ለምን አስፈለገ? ንግግራቸው ግራ ሆኖ ግራ አጋብቶኛል፡፡ በሰላማዊና ህጋዊ ሁኔታ ከሚካሄድ ምርጫ ማንም ያሸንፍ ማን ውጤትን በፀጋ መቀበል ስልጡንነት ነው - ተግባባን አቶ ሥዬ ፡፡

የአቶ ሥዬን ንግግር በጥልቀት ላጤነው ምርጫው ሰላማዊ ፉክክር እንዲኖረው ያለመ ነው ብሎ ለመቀበል እጅጉን ይከብዳል፡፡ በዚህ መሰል ተናዳፊ ቀስቃሽ ንግግር ተነሳስቶ ራሱን በእሳት ወላፈን ለመለብለብ የተዘጋጀ ተከታይ ያገኛሉ ብሎ ማሰብም ይከብዳል፡፡

የኢትዮጵያ ህዝብ ካለፉት ሒደቶች ብዙ ተምሯል፡፡ ለሠላም ጋሬጣ የሆኑ መንገዶች ላይ ላይራመድ ደጋግሞ ለራሱ ቃል ገብቷል፡፡ የነውጥና የጥፋት ቀውስ አማራጮችን ሊሸከም ትከሻውን አላደነደነም፡፡ እናስ?

ከሠላማዊና ህጋዊ የመወዳደሪያ ስርዓት አፈንግጦ ለመውጣት ለዚያ ሲባል በተዘጋጀ የጥፋት ፈረስ ላይ ተቀምጦ መጋለብ የጤና አይደለምና ተመራጭ አይሆንም፡፡

አቶ ሥዬ እርስዎም ሆኑ አንዳንድ የተቃዋሚ ፓርቲ አመራሮች በአደባባይ እየደሰኮራችሁ ያላችሁት ንግግር ቢጤን ምን ይዘት እንዳለው ግልፅ ነው፡፡ በምርጫው ዋዜማ ላይ ሆናችሁ ለምትቋምጡለት የቀለም አብዮት ማነሳሻ ይበጀናል የምትሏትን የመጀመሪያ የጥፋት ችቦ ለመለኮስ ዳር ላይ የቆማችሁ ይመስለኛል፡፡ የንፁሃንን ደም ለግብር ለማቅረብ ሽር ጉድ ማለት መልካምም አይደለም፡፡ የ97ቱን አይነት ሁከትና ብጥብጥ እንዲደገም የሚሻ ደጋፊ እንደማታገኙ ተረድታችሁ ከወዲሁ እርማችሁን አውጡ፡፡

በሰላማዊና ህጋዊ መንገድ የፖለቲካ እንቅስቃሴን ማድረግ እየተቻለ የጥፋትና የማተረማመስ ተልእኮ ላይ ቤንዚን አርከፍክፎ እሳት ለማቀጣጠል መቋመጥና ማላዘን አይበጅምና ቢቀር ምክሬ ነው፡፡

የመንግስት ስልጣን በአብላጫ የህዝብ ድምፅ ድጋፍ እንደማታገኙ ከወዲሁ ስትገምቱ ሰበብ ይዛችሁ ብቅ አላችሁ፡፡ የመንግስት ሥልጣን ላይ የሚወጣው በህዝብ ድጋፍና ከዚያ በሚገኝ ድምፅ ብቻ መሆኑን ብትገነዘቡ ምን አለ?

‹‹እኔ ካላሸነፍኩ ኮሮጆ ተገልብጦ ምርጫው ተጭበርብሯል›› ነጠላ ዜማ ዛሬ እሱ አይሰማም፡፡ ለመሆኑ አቶ ሥዬ በተንቤን ያሸነፉት የሕወኃት ፕሮግራምን ይዘው እንደሆነስ ተዘንግቶ ይሆን፡፡ በፓርላማ የነበረዎትን መቀመጫ እንዲያጡ ላደረገው የተንቤን መራጭ ህዝብ ዛሬ ምን አቅርበውለት ይሆን?

አቶ ሥዩ የአፄው ስርዓት ናፋቂ የሚያስመስልብዎ ንግግርዎን ሳዳምጥ ምን ያህል እንዳፈርኩብዎ ሳልደብቅ ልንገርዎ፡፡ በዚህ ዙሪያ ምንም ለማለት አልፈቅድም፡፡ ከምን ተነስተው የዜሮ ፓርቲ ስርዓት አድናቂ እንደሆኑ የአሁኑንና የኋላ ታሪክዎን በዚህ ፅሁፍ ለመዳሰስ አልሻም፡፡ ይሁንና እንዳማረዎት ይቀር እንደሆነ እንጂ ከዚህ በኋላስ የአፄው ስርዓት ላይመለስ ሔዷል፡፡

እነ ከድር ሰተቴን "ኢሠፓአኮ - ባዶ ፓኮ" መሰል ሚሊዮኖች የመናገር ነፃነታቸውን ተነፍገው በየጊዜው ዘብጥያ ይወርዱና ህይወታቸውን ያጡ የነበረበት ያ ክፉ ዘመንም ዳግም ላናየው እርቆ ተቀብሯል - "ኢሠፓአኮ - ባዶ ፓኮ፡፡" መልካም ጊዜ፡፡